# ❖ የምሕላ ፀሎት

ሃሌ ሉያ ለቤተክርስቲያን ስትል በአደባባይ በጥፊ የተመታሀ፡ አቤቱ ይሕን የአደረግሕ እርስዋን በከበረ ደምኅ ትቀድሳት ዘንድ ነው።

ለርስዋ ሲል ታስሮ መንገላታትን የቻለ፤ የበደለውም በደል ሳይኖር ርኩስ ምራቅ ሲተፉበት የታገሠ፡ አምላክ በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ ።

ሃሌ ሃሌ ሉያ አቤቱ ይቅርታህን አሳየን፡ ረዳት ሁነን፡ አትጣለን፤ ማረን፤ ራራልን፡ አቤቱ ይቅር በለን።

አብ ሆይ ማረን፡ ሃሌ ሉያ፡ ወልድ ሆይ ይቅር በለን፡ ሃሌ ሉያ ይቅር ባይ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፡ በይቅርታህ አስበን (3)
ለአንተን ፍጹም ምስጋና እናቀርባለን። ቸር ይቅር ባይ ሆይ ማረን። ኃጢአታችንም አስተሥርይልን ።የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ አድነን በነፍስም በሥጋም ጠብቀን።
አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይቅር በለን ።
በቸርነትህ ብዛት በደላችንን ደምስስ።
ይቅርታህንም ላክልን።
ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና።
ሃሌ ሉያ።ይቅር ባይ አብ ሆይ ማረን። ይቅር በለን። መሐሪ የሆንሕ አቤቱ ይቅርታህን ስጠን። የቀድሞ ኃጢአታችንም አስበህ አታጥፋን።
በቸርነትሕ አንተ ይቅር ባይ ነሕና።
ለሚለምኑሕ ለሚጠሩሕ ሁሉ። ይቅርታህ ብዙ ነው። በእውነት ይጠሩሃል አንተም ዘወትር ትሰማለህ ። ሁሉን ለማድረግ የምትችል ነህ።
ሁሉን ለማድረግ የሚችል አምላካችን ቃሉ እውነት ነውና። ይቅርታውን ይልክልን ዘንድ። አብን እንለምነው። አብ ለለመነው ሁሉ ይበቃልና።

ሃሌ ሉያ ።ለርሱ ምስጋና ይገባል። ሃሌ ሉያ ።ለርሱ ክብር ምስጋና ይገባል ።ሃሌ ሉያ ። ለሁሉ ጌታ ለክርስቶስ። ሃሌ ሉያ
ሃሌ ሃሌ ሉያ። ዛሬስ ተስፋየ ማነው እግዚአብሔር አይደለምን።

[አቤቱ ነፍሴን ለአንተ አደራ አስጠብቃለሁ። ከምሕረት አምላክ ዘንድ ነፍሴን አደራ አስጠብቃለሁ። ከምስጋና አምላክ ዘንድ። ነፍሴን አደራ አስጠብቃለሁ። በጌታዬ እና በአምላኬ። ነፍሴን አደራ አስጠብቃለሁ ። ከክፉ ሥራ ሁሉ ነፍሴን አድናት።](3)

ኑ እንለምነው። እንለምነው እንማልደው።
የአምላካችን ቃሉ እውነት ነውና።
ሁሉን የሚችል የሚሳነው የሌለ እርሱ ነው።
የድሆች አምላክ የአዘኑትን የምታረጋጋ።
አቤቱ እኛ ወዳንተ ተማጽነናል።
ሁሉን የሚችል የሚሳነው የሌለ እርሱ ነው።
የድሆች አምላክ ተስፋ ላጡ ተስፋ የምትሆን አቤቱ እኛ ወዳንተ ተማጽነናል
ሁሉን የሚችል የሚሳነው የሌለ እርሱ ነው።
የድሆች አምላክ ረዳት የሌላቸውን የምትረዳ አቤቱ እኛ ወዳንተ ተማጽነናል።

ሁሉን የያዝክ እግዚአብሔር አብ ሆይ ማረን።ተቀዳሚ ተከታይ የሌለህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይቅር በለን።የእውነት መንፈስ ጰራቅሊጦስ ሆይ ኃጢአታችንን አስተሥርይልን።
በችግርና በሐዘን ጊዜ ረዳት የለንምና፡ ያለአንተ ሌላ አናውቅም፡ አምላኪየ አምላኪየ ብለህ በጮኽከው ጩኸት ተማጽነናልና፡ አምላካችን ሆይ ልመናችንን ተቀበል።
[ከጡአት እስከ ማታ እንደጠበቅከን አቤቱ እንዲሁ ከማታ እስከ ጡአት ጠብቀን።](3)